# ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አንድነት

## ጌታቸው ኃይሌ

"እናት ቤተ ክርስቲያናችን አልተከፈለችም" በሚል ርእስ ጽፌ ፥ ሰኞ ጥር 6 ቀን 2004 ዓ. ም. (ጃንዋሪ 28 2013) በኢትዮሜዲያ ባሳተምኩት ድርሰቴ ውስጥ ቀኖናን የተደገፈ አስታራቂና አቀራራቢ ሐሳብ ሳቀርብ ፥ የአዲስ አበባውም የአሜሪካም ሲኖዶስ ሕገ ወጥ ከመሆናቸው ተነሥቼ ስለሆነ ፥ ከዚህም ከዚያም ፥ አንዳችም ተቃዋሚ አይነሣም ብየ አላሰብኩም ። እንዲያውም የተቃዋሞዎቹ ቍጥር ማነሱ ገርሞኛል ። ሊገርመኝ ሳይገባ የገረመኝ ፥ ሁለቱ የተቃውሞ መልሶች አማራጭ ሐሳብ ከማምጣት ወይም የኔን የሐሳብ ድክመት ከማሳየት አልፈው ፥ ከርእሱ የወጡና ራስን ከአንባቢ ትዝብት የሚጥሉ ቃላት መያዛቸው ነው ። መቼ ይሆን ሐሳብ ለሐሳብ ማፋጨትና የተሻለውን መያዝ የምንችለው ? መቼ ይሆን "ኵሎ ፡ አመክሩ ፡ ወዘሠናየ ፡ አጽንዑ ፡" ያለውን የቅዱስ ጳውሎስ ምክር የምንሰማው? ሌላ ሁለት ሺሕ ዓመት ሊያስፈልገን ይሆን? ያውም በምዕራቡ ዓለም እየኖርንና በዩኒቨርስቲዎቹ እያስተማርን!

አሁን ልጽፍ የተነሣሁት ፥ ወዳጄ መምህር ከበደ አገኘሁ ዘውእቱ ስምአ ጽድቅና ዶክተር ዋለ እንግዳየሁ (Walle Engedayehu, Ph.D.) ለኔ መልስ በሰጡባቸው ጽሑፎቻቸው ውስጥ አንደኛ ፥ ስለ እኔ ሲጽፉ ያልሆኑትን ነገሮች ሆነዋል እያሉ የደጋገሟቸውን ለማስተባበል ፥ ሁለተኛ ፥ ያሳሳቱትን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለማረም ነው ። በዚህ አጋጣሚ ፥ ታዛቢ (መንግሥቱ ሙሴ) ኢካድፎረም ላይ "አንድነታችን ከእምነት ቤታችን ይጀምራል" በሚል ርእስ የኔን የሐሳብ ድክመት እንደታየው በማሳየት ያወጣውን ድርሰት ማድነቄን ልገልጽ እፈልጋለሁ ። ችግራችን ከተሰማው ሰው የተጻፈ ስለሆነ እንዳስብበት አድርጎኛል ።

### መምህር ከበደ ፩

1. መምህር ከበደ ወደ ታሪክ ሄዶ "ለ1600 ዘመን የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ የመራን በመንፈስ እንጂ በአካል ኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ መካከል ሆኖ ነበር? ለምን ይሆን ከኞቹ ላይ ሲሆን ይህ አሠራር የሚነቀፈው? ምሥጢሩ ምን ይሆን? ብሎ ይጠይቃል ። ምሥጢሩ ግልጥ ነው ። በዚያን ጊዜ ፥ ኢትዮጵያ ያንድ ፥ ግፋ ቢል የሁለት ፥ ሊቀጳጳስ (ሜትሮፖሊታን ፥ ሙጥራን) ሀገረ ስብከት ነበረች ። የነገረ መለኮት ጭቅጭቅ ወይም ሌላ የቤተ ክርስቲያን ችግር በተነሣ ቁጥር እጨጌው ፥ ንጉሡ ፥ አበምኔቶች ጉባኤ እያደረጉ መፍትሔ ይፈልጉ ነበር ።
   እግረ መንገዳችንን ታሪክ እንድንማር አፄ ዘርአ ያዕቆብ ያደረገውን ልንገራችሁ ።

   ወዓዲ ፡ አዘዝኩ ፡ [አነ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብ ፡] በከመ ፡ አዘዙ ፡ ሐዋርያት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ጉባዔ ፡ ለአርትዖ ፡ ሃይማኖት ፡ ወረክብ በ፳፭ ዕለት ፡ እምፋሲካ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ መንፈቀ ፡ ጰንጠቈስጤ ። ወካዕበ ፡ ይኩን ፡ ጉባኤ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ለወርኃ ፡ ጥቅምት ፡ በከመ ፡ አዘዙ ፡

ሐዋርያት ፡ በሲኖዶሶሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ቅሩበ ፡ ሀገረ ፡ ጳጳስ ። ወእለኒ ፡ ይነብሩ ፡ ቅሩበ ፡ ተዓይነ ፡ ንጉሥ ፡ ይትጋብኡ ፡ ውስተ ፡ ተዓይነ ፡ ንጉሥ ። ወእለሰ ፡ ይነብሩ ፡ ርኁቀ ፡ ይግበሩ ፡ ጉባኤ ፡ ኀበ ፡ ዓበይት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ።

ደግሞ ሃይማኖት ለማርታትና ለረክብ ፥ ከፋሲካ ጀምሮ በ 25ቀን ፥ ማለት የጰንጠቈስጤ አጋማሽ ላይ ፥ ጉባኤ ይደረግ ዘንድ ሐዋርያት እንዳዘዙ ፥ [እኔ ዘርአ ያዕቆብ] አዝዣለሁ ። እንዲሁም ፥ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዳዘዙ ፥ በጥቅምንት 12 ቀን ፥ ጉባኤ ይደረግ ። ለጳጳሱ ከተማ (ሜትሮፖሊት) ቅርብ የሚኖሩ [ካህናት በጳጳሱ ከተማ] ፥ ለቤተ መንግሥቱ ቅርብ የሚኖሩ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ይሰብሰቡ ። በሩቅ የሚኖሩ ደግሞ በካቴድራል አብያተ ክርስቲያን ይሰብሰቡ ።

ካህናቱ መፍትሔ ከግብጽ ፓትርያክ ሲፈልጉ ፥ ጥገኝነታቸውን በማመን ነው ። ወደኛ ሁኔታ ስንመጣ ፥ ድዮስጶራው የታላቋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት ነው ። ታላቋን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በድዮስጶራው ስር ያለች ሀገረ ስብከት (የተገላቢጦሽ) አታድርጋት ።

2. "ሲኖዶስ ማለት የጳጳሳት ጉባኤ መሆኑን ከተስማማን ታዲያ በዚህ በአዲስ አበባ ውስጥ ባለው ሲኖዶስ የተሰበሰቡት ጳጳሳት ተጨቁነናልና ነፃ አውጡትን የሚል ጥሪ መች ለእኛ ለድያስጶራዎች የድረሱልን ጥሪ አቀረቡ?"
ምን ዓይነት ጥያቄ ነው? ሎስ አንጀለስ ላይ የተሰበሰበው ሲኖዶስ መግለጫ ፥ "ቀደም ሲል ለቀኖና ቤተ ክርስቲያን መፋለስ ምክንያት የሆነውና ቅዱስ ፓትርያርኩን በግፍ ከመንበራቸው ያሳደዳቸው ኃይል ፡ አሁንም የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ክብር አለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን ፡ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማጥፋት ትውልድንም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማዳከም ቆርጦ የተነሣ ኃይል . . . ነው" ማለቱን አልሰማህም ፥ ወይስ መግለጫ ያወጡትን ዋሾዎች ልታደርጋቸው ፈልገህ ነው? "ሐሰ!" እንዲያውም ፥ ዶክተር ዋለ ከእኔ የበለጠ ስላብራራው ገጽ 2 ላይ ያለውን አንብብለት ።

3. "ምነው ፕሮፌሰር . . . እነሱ የተወለዱበት መንደርም እኮ ቢሆን የርሳቸውም ነው ። እርሳቸው የተወለዱበትም እንዲሁ የነርሱ ነው" አልከኝ ።
ምነው ወዳጄ "ስምአ ጽድቅ" ፥ የጎጠኝነት ጉዳይ አደረግኸው? ዶክተር ዋለንም እንዲሁ ትለው ይሆን? ወይስ እሱን የምትምርበት ምክንያት አለህ? እንዲህ ያለው አነጋገር እኮ የተናጋሪውን ክብደት ይቀንሳል ። የታላቋ ጎንደር ልጅ ሆነህ የወያኔ የጎጠኝነት በሽታ ከምን አገኘህ? ስለዚህ በሽታ ፥ "ከበደ ፡ ኢትርሳዕ ፡ ዘተዋነይነ ፡ ክልኤነ ፡ እንዘ ፡ አንተ ፡ በኦሪጎን ፡ ወበሚኒሶታ አነ ።"

4. "ሲኖዶሱን ደግፈህ ኢትዮጵያን ሬጅስተር ላይ ጽፈሃል ።"

ተቀድመሃል ። የሚያሳስት ነገር ከማከብራቸው ሰዎች ሰምቼ ተሳስቻለሁ ብያለሁ ። ንስሐን የማያውቅ ስሕተትን ማመን አያውቅም ። ሃፍረት ይመስለዋል ። ስለዚህ ይሆን መናዘዜን ማመን ያቃተህ? የአንድነታችን መፍትሔ ስሕተትን አምኖ መንገድን ማስተካከል ነው ።

Walle Engedayehu, Ph.D.

ስዱዳን ካህናት ሲኖዶስ በማቋቋማቸው የተፈጠረውን ችግር ፈጣሪዎቹ ምን እንደሚሉ ለማወቅ የፈለገና ነገር መደጋገም ያረዘመውን ጽሑፍ ለማንበብ ጊዜ ያለው ካለ ፥ የዶክተር ዋለ ፌብሩዋሪ 2 ፥ 2013 ዓ. እ. ኢትዮሜዲያ ላይ ያወጣውን ማንበብ ይችላል ። ድርሰቱ ያተኮረው በእኔ ድርሰት ላይ ስለሆነ ማንበቤ የሚጠበቅ ነው ። አንድ ጉዳይ ሲተች አለመስማማት የተለመደ ስለሆነ ፥ የማንስማማባቸውን ነጥቦች ትቼ ፥ ስሕተቶቹን ብቻ ለማረም እሞክራለሁ ።

ራቅ ብየ ሳልሄድ ፥ ዶክተር ዋለ በዛሬ ድርሰቱ ለኢትዮጵያ ጥናት ያደረግሁትን አስተዋፅኦ ማወቁ አዲስ ነገር ቢሆንብኝም ፥ አመሰግናለሁ ። ሁለተኛም ፥ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ የመንግሥት ጭቁን ነው ያልኩትን ለማስተባበል ለሞከረው ለመምህር ከበደ ከኔ የተሻለ መልስ መስጠቱን ወድጀዋለሁ ። አሁን ወደቅሬታዬ በዝርዝር ልሂድ ፤

1. የዶክተር ዋለ ድርሰት ያተኮረው ፥ ርእሱም እንደሚያመለክተው ፥ የገለልተኝነት (neutrality) ጎጂነት ላይ ነው ። ገለልተኝነትን ደግፎ የተናገረ ሰው ካለ ፥ ምክሩን ሊያዳምጥ ይችላል ። ከኔ ሐሳብ ጋር ግን ፥ ከሚያስፈልገው በላይ ካልጎተቱት ፥ ሊገጥም አይችልም ። ገለልተኝነት ከዳር ቆሞ ፥ "አሸነፈው ፤ ተሸነፈ" ማለት ነው ። ይኸ ዓይነት ሐሳብ ልጽፈው ቀርቶ አላሰብኩትም ። ምናልባት አጻጻፌ ግልጽ ባይሆን ይሆናል ፥ ዶክተር ዋለ ለመቃወም ብዙ (አንዳንዶቹም ትርፍ) ቃላት እንዲጠቀም የተገደደው ። ለማለት የሞከርኩት ፥ የድዮስጰራው ካህናት ባንድ በኩል ቀኖናዊ ፥ በሌላ በኩል አስተባባሪ ሲኖዶስ አቋቁመው መንፈሳዊ አገልግሎት ይስጡን ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ፥ "እስመ ፡ ቀትልክሙ ፡ ኢኮነ ፡ ምስለ ፡ ዘሥጋ ፡ ወደም ፡ ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ መኳንንተ ፡ ጽልመት ፡ [ልቡሳነ ፡ ሥጋ] አጋንንት ፡ እኩያን ፡ እለ ፡ መትሕተ ፡ ሰማይ ፡" እንዳለው ፥ ተባብረን ትግላችንን ሲኖዶሱን ከጨቆኑት ሥጋ- ለበስ የአጋንንት ኀይላት ጋር እናድርገው እንጂ ፥ ከጭቁኑ ሲኖዶስ ጋር አይሁን ነው ። ዶክተር ዋለ አነጋገሬ ባይገባው ነው ይህ ሐሳብ እኛን የአመራር ሥርዓት አልባ (devoid of a hierarchical order) ያደርገናል ለማለት የበቃው ።

2. ዶክተር ዋለ እንደሰደበኝ ተሰምቶታል ። ማስረጃውን ሳይሰጥ divisive, controversial, embodiment of division የሚሉ ቅጽሎች መስጠቱን harsh ብሎታል ። ማስረጃ ቢሰጠን ኖሮ ተገቢ እንጂ ክፋት አይኖርበትም ነበር ። ስላልሰጠ ግን ክፋት አለበት ፤ ምንም ሳላደርገው ስለሰደበኝ ሕሊናው

እንቅልፍ እንዳያሳጣው የደገፋቸው ካህናት ይጸልዩለት ይሆናል ። ሆኖም ፥ ከሰው ጋር የሚያጋጨኝን እሱ ማንሣት ከከበደው ፥ እኔ ልሸከምለት ፤

<u>አንደኛው ፥</u> የትግሬ ወያኔዎች (Tigrai People's Liberation Front) በምርጫ ሳያሸንፉ ሥልጣን መያዝ አይገባቸውም በማለቴ ደጋፊና ተቃዋሚ አስነሥቻለሁ ። ወያኔዎች ብዙ ጽፈውብኛል ። "ከወያኔ ጋር ሁን ፤ ከነሱ ጋር አትጣላ ከሚል ሰው በቀር ፥ divisive ሊለኝ አይችላል ። እኔ ግን ወያኔዎች ወገናቸው ከሚያደርጉኝ ፥ ዶክተር ዋለ እንደነሱ divisive ቢለኝ እመርጣለሁ ።

<u>ሁለተኛው ፤</u> ዜናሁ ለጋላ የሚባለውን የአባ ባሕርይን ድርሰት ተርጉሜ ማብራሪያ ጨምሬ በማሳተሜ መጀመሪያ ነፍሱን ይማርና የግዕዝ ቋንቋ መሃይምኑ ዶክተር ዓለሜ እሸቴ እኔን በግዕዝ ላይ ብዙ የሠራሁትን ሰው ፥ "ያስተረጎምኩትን ወሰደብኝ" ብሎ በሕዝብ ፊት ሲሰድበኝ መልስ ሰጥቼ ነበር ። ዶክተር ዋለ divisive የሚለኝ ይኸንንም በማስታወስ ነው ። የሆነውን ዶክተር ዋለ ረስቶት እንደሆነ ፥ በዚያን ጊዜ እንዳጋጣሚ ስለ ሲኖዶስ ጽፌ ስለነበረ ፥ ተቆጥቶ ፥ "መጀመሪያ ዶክተር ዓለሜ እሸቴ ላቀረበልህ ክስ መልስ ስጥ" ብሎ ያሳዘነኝን ላስታውሰው ። ቀጥሎ ፥ ኦሮሞ ነን የሚሉ ተነሡብኝ ። መጽሐፉ አዲስ አበባ እንዳይሸጥ አደረጉ ፤ ብዙም ጻፉብኝ ። እንገድልሃለን እስከማለት ዛቱብኝ ። ለወጣቱ የሀገሩን ታሪክ በማስተማሬ ሰዎች ሲሰድቡኝ ፥ እንደ ሀገር ወዳዶቹ በመደገፍና በማበረታታት ፈንታ divisive, controversial, embodiment of division የሚሉ ቅጽሎች መስጠ ከፋትና የኢትዮጵያ ታሪክ እንዳይታወቅ መሰናክል ከሚፈጥሩ ወገኖች ጋር መሰለፍ ነው ።

<u>ሦስተኛ ፤</u> ሲኖዶስ አይሰደድም የሚል አቋም በመያዜ ብዙዎች እንደዶክተር ዋለ ተቃውመውኛል ። እኔ divisive ከሆንኩ ፥ ይሰደዳል የሚሉትንም ፥ ራሱን ዶክተር ዋለን ጨምሮ divisive ማድረጉ ለዶክተሩ አልታየውም ። በእምነቱ የጸና ሰው በእምነቱ ወስጥ ያለ ስሕተት (የዓይኑ ጉድፍ) አይታየውም ።

የሰደብከኝ እዚህ በዘረዘርኳቸው ምክንያት ሳይሆን ፥ በሌላ ምክንያት ከሆነ ፥ ስሕተቴን እንዳውቅ ንገረኝ ፤ አለዚያ አትሳደብ ፤ ነውር ነው ። የማንን ከፋፋይነት እኔ ላይ ልትለጥፍ አስበሃል?

3. ወደመጨረሻው ነጥቤ ከመምጣቴ በፊት ለዶክተር ዋለ ሁለት አነጋገሮች ላርምለት ፤ 1. ልኡካን ካህናት በሚያገለግሉት ሕዝበ ክርስቲያን ታጭተው ጳጳስነት ይሾማሉ (consecrated) እንጂ ፥ እንደ ወታደር አይመለመሉም (conscripted). 2. ማናችንም ከየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ማስቀደስ መቻላችን እውነት ነው ። ሁኔታውን በነገረ መለኮት ምክንያት ከተከፋፈሉ ከነMethodis, Baptist, Lutheran, Anglican Prespiterian ጋር የሚያመሳስል አላዋቂ ነው ። ". . . the Church has been divided for more than two decades, because of doctrinal issues" ያለው ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አፍ አይወጣም ።

ዶክተር ዋለ ፤

እስከዚህ የጻፍኩት ፥ ከዚህ በታች የምጠቅሰውን ያህል አያጋልጥህም ። "unbecoming of a scholarly figure" ያልከኝ የኔ ሐሳብ አንተ ከምትደግፈው ሐሳብ ጋር ስላልተስማማ <u>ብቻ</u> ነው ። ይህ ከሆነ ፥ ያንተ ሐሳብ እኔ ካቀረብኩት ሐሳብ ጋር ስላልተስማማ "unbecoming of a scholarly figure" እንደሚያሰኝህ አልታየህም ። "unbecoming of a scholarly figure" የሚባለው እንዳንተ ያለ ምሁር የሚናገረውን ሳያጣራ ሲናገር ነው ። ይኸን ያልኩበትን ለማስረዳት ስጠቅስህ እንዳልሳሳት በጥሞና ተከተለኝ ፤

> "Dr. Getachew (sic) reportedly reconciled his past estrangement with the General Secretary of the Synod, requesting for the latter's forgiveness, which was a gracious and novel move thing to do on the part of the professor " (p. 4).

General Secretary of the Synod ያልከው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን ነው ፤ አይደለም? በብፁዕነታቸውና በእኔ መካከል አለመግባባት መኖር የለበትም የሚሉ የሀገር ሽማግሌዎች ሁለታችንን ለዕርቅ ማገናኘታቸው እውነት ነው ። ሁለታችንም ሽማግሌዎቹን አመስግነን ጸሎታችንን ብፁዕነታቸው ለንጉሡ ሰላም አሳርገውልን ተለያይተናል ። ግን ከዕርቁ በፊት ብፁዕነታቸው ለምን በይፋ እንደወረፉኝ መጀመሪያ ለማወቅ ፈልጌ ነበር ። ሽማግሌዎቹ ፥ "ወደኋላ ከሄድን ከዕርቁ ይልቅ ጥሉ እየከረረ ስለሚሄድ ፥ የምንመርጠው ይቅር ለእግዚአብሔር ብላችሁ ብትታረቁልን ነው" ስላሉኝ ፥ ቃላቸውን በማክበር ፥ ለምን እንደተጣላን ከብፁዕነታቸው ሳልሰማ ታረቅን ። አሁን አንተ የምትለው እኮ ፥ (በእኔ ቃላት ልግለጸውና) ስለሲኖዶስ መጻፍንም ሆነ መናገርን የሲኖዶሱ ጸሐፊ የግል መብታቸው አድርገውት ፥ አንተ በመጻፍህ ተጣላችሁ ነው ፤ አይደለም? ከምን አገኘኸው? ምክንያቱ እሱ ከሆነ ፥ ታዲያ አንተ ስለሲኖዶስ ስትጽፍ ለምን አልተጣሉህም? እባክህ ፥ ብዕርህን በመንፈስ እየጸፉ የሚጽፉበት አታድርጋቸው ። ለማንኛውም ፥ ያለነው የሌላውን መብት የማይነካ ሐሳብ የመጻፍ መብት በተከበረብት ሀገር ነው ። ባዘጋጁት መድረክ ፥ በሚቆጣጠሩት ቤተ ክርስቲያን እንዳልናገር ይከለክሉኛል እንጂ ፥ ኢንተርኔትን በውግዘትም አይነኩት ።

ብፁዕ አቡነ መልከጼደቅ የተጣሉኝ እውነት በዚህ ምክንያት ከሆነ ፥ በሐሳብ መለያየት የማያጣላ መሆኑን አጥተውት ሳይሆን ፥ በአሜሪካ ሲኖዶስ ለማቋቋም ያወጡት ፈለግ በቀኖና ቊልፍ የተዘጋ መሆኑን ስላሳየሁ ሊሆን ይችላል ። ለማንኛውም ፥ ከብፁዕነታቸው በቀጥታ ሳልሰማ ፥ በይሆናል ከዚህ የበለጠ መናገር ፥ ያንተ ብጤ ያደርጋል ። ይህን ድርሰት በሕዝብና ዕርቅ ባወረዱልን ሽማግሌዎች ፊት እንድትመልሰው በሚገባህ በጥያቄ ልደምድመው ፤ በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅና በእኔ መካከል ስለተደረገው ዕርቅ ዝርዝር የጋራ መግለጫ አላወጣንም ። ለዕርቅ ከአነጋገሩኝ ከአራት ሽማግሌዎችና በኋላ ብፁዕነታቸው ከአንድ ካህን ጋር ከመምጣታቸው በቀር ፥ ዕርቁ ሲካሄድ በክፍሉ ውስጥ ማንም ሌላ ሰው አልነበረም ። ከእነሱ ውስጥ ማነው አስቀድሜ ብፁዕነታቸውን ይቅርታ መጠየቄን ዋሽቶ የነገረህ? ወይስ የምሁር ስም ይዘህ reportedly እያልክ ፥ የሰው ክብር የሚነካ አሉባልታ በዓለም ዙሪያ ትበትናለህ?